**ETHIOPIAN CUSTOMS AUTHORITHY**
**የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት**
**ADDIS ABABA KALITY CUSTOMS BRANCH OFFICE**
**የውስጥ ማስታወሻ /INTER OFFICE MEMO/**

ቁጥር፡ ስ/አ/ጽ/ቤት 21/2011

ቀን፡ ጥቅምት 07 ቀን 2011 ዓ.ም

- ለ፦ ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ስ/ሂ
- ለ፦ ኢስተርን ኢንዱስትሪ ዞን ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ስ/ሂ

- ከ፦ ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
  ስ/አ/ቃ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት፣

አዝዘው ጫኔ አበበ
ስራ አስኪያጅ
Azizew Chanie Abebe
Manager

ጉዳዩ፦ **የኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ የአሠራር ስርዓት መሻከን ይመለከታል፣**

ከጉምሩክ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር በቁጥር 4.0/105/11 በቀን 05 ጥቅምት 2011 ዓ.ም በጻፈልን ደብዳቤ መሠረት በኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ላይ የሚስታወሉ የግልፀኝነት ችግሮች በተመለከተ በተለያየ ጊዜያቶች ከቅ/ጽ/ቤቶች ጥያቄዎች ሲነሱ የቆዩ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ችግሩን ለመቅረፍና ሲነሱ የነበሩ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ዕቃዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሲገቡ፣ ሲወጡ እና ሽያጭም ሆነ ምርት ሂደታቸውን ለማጠናቀቅ ከፖርኩ ወደ ሌላ ፓርክ ለመውሰድ ጥያቄዎች ሲቀርቡ የጉምሩክ አሠራር ሥርዓት ተልኮልናል።

በዚሁ መሠረት የተላከውን ማንዋል 17 ገጽ አያይዘን የላክንላችሁ በመሆኑ በተላከው ማንዋል መሠረት ተፈጻሚ እንዲሆን አሳውቃለሁ።

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፦
- ለ፦ም/ሥራ አስኪያጅ /ሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ዘርፍ/
- ለ፦ም/ሥራ አስኪያጅ /የጉምሩክ ጉዳዮች ዘርፍ/
- ለ፦ህግ ማስከበር ም/ስራ አስኪያጅ
- ለ፦ ሕግ ማስከበር የስራ ሂደት
- ለ፦ ጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ
- ለ፦ ጉምሩክ /ሥ/ሥ/አ/የስራ ሂደት
- ለ፦ መጋዘን አስተዳደር ቁጥጥር የሥራ ሂደት
- ለ፦ ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የስራ ሂደት
- ለ፦ ደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደት
  አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

# የኢንድትሪ ፓርክ የጉምሩክ አሠራር ሥርዓት

ጥቅምት/2011

አድስ አበባ

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

1. መግቢያ

ሀገራት በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ለመሆን እና ለሚያመርቷቸው ምርቶች ሰፊ ገበያ ለመፍጠር የተለያዩ የማበረታቻ ስርዓቶችን በመቅጽ ተግባራዊ ያደርጋሉ።

በሀገራችንም ቀደም ሲል ከተዘረጋው የኤክስፖርት የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ከተጠቀሱት መካከል የኢንዱስትሪ ፓርክ/ዞን/ እንደ ሥርዓት የተቀመጠ ቢሆንም የአሠራር ሥርዓት ያልተቀመጠ በመሆኑናየሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የበለጠ ለማፋጠንና ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለመሸጋገር የተለያዩ ኢንዱስትሪ ፓርኮች በመገንባት ወደ ስራ እንዲገቡ እየተደረገ ይገኛል።

እነዚህ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለሀገራችን ከሚያስገኙት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ መካከል የስራ እድል ፈጠራ፣የቴክኖሎጂ ሽግግር፣የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ከመሆን ባሻገር የገቢ ዕቃን በሀገር ውስጥ ምርት መተካትንም ያጠቃልላል።

በመሆኑም የአገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት እና ልማትን ሊያፋጥኑ የሚችሉ አሰራሮችን ለመዘርጋት እና ለሀገር ውስጥም ይሁን ለውጭ ባለሀብት ሳቢ እና ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር 886/2007 ወጥቷል።

በተጨማሪም የተሻለ ግልጽነት እና ተጠያቂነት እንዲኖር ብሎም የተቀናጀ እና የተሳለጠ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል ለኢንዱስትሪ ፓርኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 417/2009 ወጥተዋል።

ባለሥልጣን መ/ቤቱም እነዚህን የሕግ ማእቀፎች እና የተለያዩ ሀገራት ልምድን መነሻ በማድረግ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሊያስፈጽማቸው የሚገቡ ተብለው በደንቡ እና በመመሪያ ውስጥ የተለዩ ዋና ዋና ተግባራትን በመለየት ግልጽ የሆነ የአሰራር ስርዓት በመቅርጽ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

በዚህም መሠረት በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ መስፈርቱን አሟልተው ወደ ስራ ለገቡ ባለሀብቶች የመብት ተጠቃሚነት ፈቃዳቸውን በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ ማዋላቸውን የሚያረጋግጥ የቁጥጥር እና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ሂደትን ያካተተ የአሰራር ሥርዓት ተዘጋጅቷል።